የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.12
ADDIS ABABA 13th January, 2017

አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፱/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለሀሙሲት - እስቴ የመንገድ ፕሮጀክት ማሰፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …………………………………..……ገጽ ፱ሺ፭፻፱

Proclamation No. 989/2017

the Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for financing the Hamusit-Estie Road project, Ratification Proclamation ……..……….………….. ...Page 9509

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፱/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሀሙሲት - እስቴ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፲፭ ሚሊዮን (አሥራ አምስት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.አ.አ ጁላይ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፮ በካርቱም ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 989/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

WHEREAS, a Loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 15,000,000.00 (fifteen million) United States Dollar for financing the Hamusit-Estie Road project, was signed in Khartoum on the 13th day of july, 2016;

WHEREAS, the House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 27th day of December, 2016;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ " ለሀሙሲት - እስቴ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፱/፪ሺ፱ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.አ.አ ጁላይ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፮ በካርቱም የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፭ ሚሊዮን (አሥራ አምስት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "the Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for financing the Hamusit-Estie Road project, Ratification Proclamation No 989/2017."

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed in Khartoum on the 13th day of July, 2016, between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 15,000,000.00 (fifteen million) United States Dollars in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall in to force on the date its publication in the Federal Gazette.

Done At Addis Ababa, this 13th day of January, 2017

**MULATU TESHOME (Dr)**

**PRESIDANT OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**